# ከመጋቢው ለመጋቢው

# «...መሪዎች ስለ መሩ ... እግዚአብሔርን አመስግኑ» (መሳ. 5:2)



ፓስተር አስፋው በቀለ
ካናዳ

# 1
# አመራርህ ወሳኝ ነው

**« . . . መሪዎች ስለ መሩ . . . እግዚአብሔርን አመስግኑ» (መሳ. 5:2)**

የድርጅቶችን ስኬት የሚያጠናና የሚያማክር አንድ ታላቅ ሰው እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበለት፡- «ወደ አንድ በፍጹም ሊሻሻል ወደ አልቻለና ወደ ተመሰቃቀለ ድርጅት ውስጥ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ጥሪ ተ ደርጎልህ ብትሄድ መጀመሪያ የምታደርገው ነገር ምንድን ነው?» መልሱ፡- «ብዙውን ጊዜ የድርጅቱን ዋና መሪ ነው ከሥራ የምናባርረው» የሚል ነበር፡፡ በመቀጠልም፣ «በመጀመሪያ እኮ መሪው ተግባሩን በሚገባ መወጣቱንና አለመወጣቱን ለማወቅ እሱን ማነጋገር አለብህ» በተባለ ግዜ የሰጠው መልስ «መሪው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ድርጅቱ እዚያ ደረጃ ባልደረሰ ነበር» በማለት መለሰ፡፡

ይህ ሰው ከሰጠው መልስ በመነሳት ስኬት ያጣ አገልግሎት መፍትሄው መሪውን መሻር ነው ወደሚል ጭፍን አመለካከት መመራቱ ማስተዋል አይደለም፡፡ ነገር ግን የዚህ ሰው አመለካከት አንድ ችላ ልንለው የማይገባንን እውነት ያስታውሰናል፡፡ የአንድ አገልግሎትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን እድገት የሚወሰነው በመሪው ነው፡፡ ለምሳሌ ሁለት መሪዎችን እንመልከት፡፡ ሁለቱም የማይተናነስ ቅባት አላቸው፡፡ ሁለቱንም ጌታ መርቷቸው ነው አገልግሎቱን የመሠረቱት፡፡ ሁለቱም ጅማሬያቸው መልካም ነው፡፡ ሁለቱም ራሳቸውን በጌታ ፊት በመመርመር በቅድስናና በፈሪሃ-እግዚአብሔር ይመላለሳሉ፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የአንደኛው አገልግሎት ሲሳካለትና ሲሰፋ፣ የሌላኛው ግን ወደታች ሲያሽቆለቁል ይታያል፡፡ ይህ ለምን ይሆናል?

መቼም የአንድ የማያድግ አገልግሎት የችግሩ መንስኤ ሁል ጊዜ በመሪው ላይ ነው በማለት መደምደም ባይቻልም፣ አንድ እውነት ግን አለ፡- በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መሪውን ይመለከተ ዋል፡፡ ሁኔታው መሪውን በቀጥተኛ መንገድ ይመለከተዋል የምንለው ችግሩ ከመነሻው ከመሪው ሲመነጭ ነው፡፡ ሁኔታው ደግሞ መሪውን በተዘዋዋሪ መንገድ ይመለከተዋል የምንለው ደግሞ ችግሩ የተነሳው ከሌላ አቅጣጫ ሆ ሳለ መሪው አያያዙን በማያውቅበት ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህም ስኬታማ መሪ በቅድሚያ ከእርሱ የሚመነጭ ችግር ራእዩን እንዳይገድልበት የሚጠነቀቅ፣ በመቀጠልም ከሌሎች ሰዎችም ሆነ ከሁኔታዎች የሚነሳን ችግር በቁጥጥር ስር ለማዋል ብቃት ያለው መሪ ነው፡፡

አመራርን፣ በተለይም ክርስቲያናዊ አመራርን ለጭንገፋ አጋልጠው የሚሰጡን ሁኔታዎች ከመጥቀሴ በፊት በስኬት ላይ ያለንን የተሳሳተ አመለካከት እንድናጠራ የሚከተሉትን ሃሳቦች ልሰንዝር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስኬት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ሳንረዳ እንችላለን፡፡ ስለዚህም ተሳክቶልናል ብለን ብዙ ጎዳና ከተ ጓዝንና ለብዙ ድካም ከተጋለጥን በኋላ ነው የምንባንነው፡፡ ከዚህ ሁኔታ ለመዳን በቅድሚያ ስኬት ያልሆኑትን ነገሮች ማወቁ መልካም ነው፡፡

1. *ቅባት፡፡* መቀባት ማለት ስኬት ማለት አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብዙ የተቀቡ ነገር ግን መጨረሻቸው ያላማረ መሪዎችና አገልጋዮች አሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ስለተቀቡና የእግዚአብሔር ኃይል ስለወረደባቸው የተሳካላቸው ይመስላቸዋል፡፡ ስለዚህም የአመራር ስልታቸውን ሳይገመግሙ፣

ከቃሉና ልምዱ ካላቸው ሰዎች ለመማር ራሳቸውን ሳይከፍቱ ዝም ብለው ይገሰግሳሉ፡፡ ሳኦል የዚህ ምሳሌ ነው፡፡ ተቀብቷል ነገር ግን አመራሩን አላወቀበትምና አልተሳካለትም፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች የሚባንኑት ሁኔታዎች ሊታደሱ እንደማይችሉ ሆነው ከተበላሹ በኋላ ነው፡፡ አእምሯቸውም በጥያቄ ይሞላል፡- «ጌታ ከቀባኝ፣ ለምን አልተሳካም?» ችግሩ ግን ቅባቱ ላይ አይደለም፡፡ ችግሩ ያለው የአመራር ስልት ላይ ነው፡፡

2. *በራእይና በድምጽ አገልግሎትን መጀመር፡፡* ከጌታ ራእይን መቀበልና በተለያዩ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች አማካይነት ማረጋገጫ ማግኘት በራሱ ስኬት እንደሆነ የሚያስቡ ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ እዚህ ላይም የሳኦል ምሳሌነት ሊታለፍ የማይቻል እውነት ነው፡፡ ሳኦል በድምጽና ከነቢይ በመጣ የማያወላውል ትንቢታዊ ማረጋገጫ አገልግሎት የጀመረ ሰው ነው፣ ነገር ግን አልተሳካለትም፡፡ አሁንም ችግሩ ያለው አመራሩ ላይ ነው፡፡

3. *ሞቅ ያለ ጅማሬ፡፡* ሞቅ ያለና ደስ የሚያሰኝ ጅማሬም ስኬት አይደለም፡፡ ስኬት ከጅማሬ ጋር ሳይሆን ከፍጻሜ ጋር የሚያያዝ ቃል ነው፡፡ እንደውም ይህ አጥብቀን ልንፈራው የሚገባን ሁኔታ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለንበት ዘመን በወረትና በጊዜያዊ ማሟሟቅ የተሞላ ክፉ ዘመን ስለሆነ ነው፡፡ ሳኦል እኮ አገልግሎቱን ሲጀምር ግሩም ግሩም የሆኑ ድሎችን ተጎናጽፎ ነበር፡፡ ያ ሁሉ የድል ብዛት ግን ከስኬተ ቢስነት አልጠበቀውም፡፡ ስኬትን በሚገባ ማስተናገድ ራሱን የቻለ ችሎታስ ይጠይቃል፡፡ ጊዜያዊ ስኬቶች ተጠራቅመው ነው ዘላቂውን ስኬት ወደ ፍጻሜ የሚያመጡት፡፡

4. *ተቀባይት፡፡* ራእያችንን፣ ማንነታችንና የአገልግሎታችንን ሁኔታ ሰዎች ሲቀበሉልን የተሳካልን ሲመስለን ተሳስተናል፡፡ ሰዎች እየተቀበሉንና እየወደዱን እንኳ ስኬት ከእኛ ሊርቅ ይችላል፡፡ ሳኦል መልኩ ያማረና ትከሻው የሰፋ፣ በሕዝቡም ፊት ሞገስ ያገኘ ሰው ነበር፣ ሆም ስኬት አልነበረውም፡፡ ሁኔታችንና ማንነታችን ሰውን መማረኩ ብቻ ሳይሆን ጌታንም ማስደሰቱን እርግጠኞች ልንሆን ይገባል፡፡

ታዲያ ስኬት ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይገኛል? ስኬትን እርግጠኛ የሚያደርግ ፎርሙላ አለ ብሎ ለመናገር አንደፍርም፡፡ ነገር ግን ለስኬት በርን የሚከፍቱና መንገድን የሚያመቻቹ የተፈተኑ እውነታዎች እንዳሉ እሙን ነው፡፡ ከእነዚህ እውነታዎች ዋነኛው የአመራር ስልት ነው፡፡ አንድ መሪ አገልግሎቱንም ሆነ ተከታዮቹን እሱ ራሱ ከደረሰበት ከፍታ አሳልፎ መውሰድ አይችልም፡፡ መሪ እንደጣራ ነው፡፡ ስኬት ከዚያ ጣሪያ አልፎ መሄድ አይቻለውም፡፡ ለምሳሌ ለተከሰተው ያለመሳካት ችግር ተከታዮቹን የሚወቅስ መሪ ወዲያውኑ እንዳይሳካለት ካደረጉት ችግሮቹ አንዱ ተገለጠ ማለት ነው፡፡ ይህም ችግር ተ ከታዮቹን በመውቀስ በሃላፊነት ተጠያቂ ከመሆን የመሸሽ ችግር ነው፡፡ መሪ በሚመራው አገልገሎት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ሃላፊነቱን ሊወስድ ይገባዋል፡፡ ጥፋቱ የሌሎች ሲሆን እንኳ፣ የመምከር፣ የመገሰጽና ካስፈለገም ስርአት የማስያዝ መብትና ስልጣኑን ተግባራዊ እስካላደረገ ድረስ በሃላፊነት ከመጠየቅ አያመልጥም፡፡

እንግዲህ ስኬት ማለት ምን ማለት እንዳልሆነ በመጠኑም ቢሆን ከተመለከትንና ለእውነተኛ ስኬት ጤናማ አመራር እንደሚያስፈልግ ካስተዋልን በመቀጠል የክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ አመራርን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነጥቦችን እናጠናለን፡፡

1. *ብቃት የሌላቸው ሰዎች ትልቅ ስፍራን በመሪነት ሲይዙ::* በተፈጥሮአዊው ዓለም የተመለከትን እንደሆነ የአንድ ሰው መሪነት የሚመዘኑባቸው ብዙ መስፈርቶች አሉ:: ያንን ሁኔታ ካላሟሉ መሪ አይደሉም ይባላል:: ወደ ክርስትናችን ስንመጣ ግን የተለያዩ መንፈሳዊ ቋንቋዎች የመሪን ብቃት እንዳንመዝን ይከለክሉናል:: ስለዚህም በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎች ካለብቃታቸው የመሪነትን ስፍራ ይይዛሉ:: ይህም ሁኔታ ለአንድ አገልግሎት ስኬት ታላቅ ጠንቅ ነው:: የብዙዎችን ከጌታ የመጡ ራእዮች ፍጻሜ ያባከነ ሁኔታ ሰዎች ካለብቃታቸው አመራርን ሲይዙ ነው:: አንድ መሪ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው መልካም ሁኔታዎች ሁሉ ሊኑሩት ይችላል:: ነገር ግን የአመራር ስልቱን ካላዳበረ፣ ስኬት የህልም እንጀራ ይሆናል:: መፍትሄው ግልጽ ነው:: ከሁሉ በፊት መሪው የአመራር ስልት ችግር እንዳለው ሊያውቅ ይገባል:: ከዚያም ያንን ችሎታ ለማዳበር የሚያስፈልገውን ነገር ከማድረግ ወደ ኀ ላ ሊል አይገባም:: መሪ ካለፈው ስህተተቱ ለመማር ፈቃደኛ ካልሆነና ከሌሎች ልምድና እውቀት ለመማር ክፍት ካልሆነ፣ ባለበት ሊረግጥ፣ ከዚያም አልፎ ወደታች ሊያሽቆለቁል ይችላል::

2. *ሁኔታዎች ወደ መሆን እስኪመጡ የሚጠብቁ ሰዎች መሪነትን ሲይዙ::* ይህ ሌላኛው የክርስቲያዊ አመራርን አስቸጋሪ የሚያደርጉት ጉዳይ ነው:: በተፈጥሮአዊው አለምና ሕግ መሠረት አንድን ነገር ካለመር ወደመር የሚያመጣ ምንም ጉዳይ ሥለሌለ ያ የተፈለገወ ነገር እንዲመጣ ካስፈለገ ሰዎች ሲለፉና ሲደክሙ ይገኛሉ:: በመንፈሳዊው ዓለም ግን የሌለውን ወደመር የሚያመጣ አምላክ የመሩን እውነት ሚዛን በጎደለው መልኩ የተረዳ መሪ ሁኔታዎችን ከመቆጣጠር ይልቅ በሁኔታዎች ቁጥጥር ስር ሊውል ይችላል:: እውነቱ ግን ይህ ነው:- ጌታ ማምጣት የሚፈልገውን ያምጣ፣ መሪ ግን በተ ሰጠው ጉልበትና አእምሮ ተጠቅሞ ሁኔታዎችን ወደመር ለማምጣት መትጋት አለበት:: በተግባር የማይመጡትን ነገሮች በጸሎት ማምጣት ይገባዋል::

3. *ደመዎዝ የማይከፈላቸውን ሰዎች የማነሳሳትና የመምራት ብቃትና ችሎታ የሌላቸው ሰዎች ሲመሩ::* በተፈጥሮአዊው አመራር ውስጥ ስንመለከት በደመዎዝ የሚሰሩን ሰዎች ለመምራት ቀላል ነው:: ሲሰሩ ይከፈላቸዋል፣ ሳይሰሩ ደግሞ አይከፈላቸውም፣ ካስፈለገም ከሥራ ይባረራሉ:: ስለዚህም ሰ ዎች ለዋጋ ሲሉ ተግተው ይሠራሉ:: በሰአቱ መገኘት፣ ተግባርን በጊዜው መፈጸም፣ አለቃን ማክበርና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሁሉ ለዋጋና ለእድገት ሲባል ይከበራሉ:: በመንፈሳዊው አገልግሎት ግን እንዲህ አይደለም:: ሰዎች የሚተጉት ራእዩ ከገባቸውና መሪው በሚገባ ካነሳሳቸው ነው:: ስለዚህም በዋጋ የሚሠራን ቅጥረኛና በነጻ የሚሳተፍ ፈቃደኛ ሰው ለማነሳሳት የምንጠቀምባቸው መንገዶች እጅግ ይራራቃሉ:: እንግዲህ መንፈሳዊው መሪ ካለዋጋ የተሰለፉ ሰዎችን የማነሳሳት ብቃቱ ከሌለው በፊቱ ቀላል ጎዳና አይጥብቀውም::

እንግዲህ መንፈሳዊውን አመራር ከባድ የሚያደርጉት እነዚህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ናቸው:: ወደ መሠረታዊው እውነት ስንመለስ መሪ በቅድሚያ የስኬትን ትርጉም በሚገባ ሊያውቅ ይገባዋል:: ይህን ከተ ገነዘበ በኋላ ደግሞ በአመራር ውስጥ ያሉትን የስኬት ሕጎች በሚገባ ሊገነዘብ ያስፈልገዋል:: ይህን ቢያደርግ ለስኬቱ ወሰን አይረውም::

« . . . መሪዎች ስለ መሩ . . . እግዚአብሔርን አመስግኑ» (መሳ. 5:2):: እውነት ነው፣ መሪዎች እንደሚገባ ሲመሩ ስኬትና ውጤት የእድል ጉዳይ ሳይሆን እውንና እርግጥኛ ይሆናል:: በዚህም እግዚአብሔ ር ይከብራል፣ ይመሰገናልም:: ነገር ግን ጥናታችን እዚህ ላይ መቅጨት አንችልም::

ረዘም ያለ ጥናትና ትምህርት የሚያስፈልገውን አንድ ጥያቄ ወደመመለስ ጎዳና እናመራለን፡፡ አንድን መሪ ውጤታማ የሚደርጉት የአመራር ሕጎች ምንድን ናቸው? ይህን ጥያቄ ወደሚመልሰው ክፍል በሚቀጥለው ጽሁፌ አቀርባለሁ፡፡ ለአሁን ግን በአንባቢዬ አእምሮ ውስጥ ለሚቀጥሉት ጽሁፎቼ የሚያዘጋጁትን ጥያቄዎችን ራሱን እንዲጠይቅ አሳስቤው አልፋለሁ፡፡

- አመራሬ እንዴት ነው?
- ሰዎች ይከተሉኛል?
- የአመራሬን ስልት እንደ እግዚአብሔር ቃል በየጊዜው አሻሽላለሁ?
- ስኬቴ የሚመዘነው በአመራር ብቃቴ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ?

**ይህ ጽሁፍ የተዘጋጀው በወንጌል
ማህበርተኝነት በየከተማው ቀንና ሌሊት ብዙ ዋጋ
በመክፈል አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ለሚያገለግሉ
መጋቢያን ብቻ ነው።**

**ውድ መጋቢያን ይህ ጽሁፍ የሚጠቅም ከመሰላችሁ
ተከታዩን ጽሁፎች ለመላክ እንዲያነሳሳን
የሚጠቅም አስተያየታችሁን
ከመለገስ አትከልከሉ!**

leasfaw@telus.net
Fax. 604-521-2164
Cell: 604-846-0904
Off: 604-5404486

Mailing address:
7895 Canada way
Burnaby, B.C. V3N3K8
Canada